የሰ/መ/ቁ. 139942

ቀን 27/03/2010 ዓ/ም

**ዳኞች፡-**ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘይባ ሳኒ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ለይላ ዘይኑ ተወካይ ጴቻሳ ጉርሙ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ተገቢውን ለመስራት ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

1. ጉዳዩ የቤት ክርክር የሚመለከት ሲሆን የጀመረው በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ በኮ/መ/ቁ. 63738 ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የስር ከሳሽ ያቀረቡት ክስ ይዘትም በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ሰበታ ከተማ አስተዳደር ዓለምገና ቀበሌ 02 ውስጥ ስፋቱ 395.7 ካሬ ሜትር በሆነው ይዞታ ላይ ቤት ሰርተው ተጠሪ በነበራቸው ጊዜያዊ ችግር በቤቱ እንዲኖሩ ተፈቅዶላቸው የነበረ ቢሆንም ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ተጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ለቀው እንዲያስረክቡ እንዲወሰን መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡
2. የአሁኑ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም በፍሬ ጉዳዩ የበኩላቸውን መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም የሚል ክርክር ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩም ቤቱ የራሳቸው እንጂ የአሁኑ ተጠሪ አለመሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡
3. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የተጠሪ ነው ከሚል መደምደሚያ የደረሰ ሲሆን

በዚህም አመልካች ቤቱን ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህ ውሳኔ በመቃወም ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከህግ ውጭ ውድቅ ስለ መደረጉ በፍሬ ጉዳዩም ቤቱ የአመልካች እንጂ የተጠሪ አለመሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ በተረጋገጠበት ሁኔታ በስር ፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉ በህጉ አግባብ አይደለም በማለት የተከራከሩ ሲሆን በዚህ አግባብ አቤቱታ የቀረበለት አጣሪ ችሎትም አመልካች ቤቱን ለተጠሪ በአደራ መስጠታቸው ባልተጠረጋገጠበት ሁኔታ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪ ባሉበት ማጣራት ይቻላል ዘንድ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ ተጠሪም የበኩላቸውን መልስ ያቀረቡ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል ፡፡

4. የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው አጭር ይዘት ያለው ሲሆን እኛም ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ከላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመረነው የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያሻው ዓቢይ ነጥብ በፍሬ ጉዳዩ የተሰጠው ፍርድና ትዕዛዝ ተገቢነት ከመመርመራችን በፊት ጉዳዩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ታይቶ ፍርድ መሰጠቱ ከስረ ነገር ስልጣን አንጻር በህጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን መታየት ያለበት ሆኖ አገኝተነዋል፡፡ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት የሚቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ የሚገኘው ኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ልዩ ዞን ሰበታ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 02 ውስጥ ነው፡፡ አመልካችም ነዋሪነታቸው ኦሮሚያ ክልል ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት መልስ ጉዳዩ የፌዴራል ሆኖ በውክልና በኦሮሚያ ክልል ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚታይ ቢሆንም ውክልና ሰጪው በጉዳዩ ላይ ስልጣን የለውም ማለት ስላልሆነ ከዚህ አንጻር የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም የሚል ክርክር ማቅረባቸውን ተመልክተናል፡፡

5. በመሠረቱ የስረ ነገር ስልጣን ጥያቄ በየትኛውም የክርክር ደረጃ የሚነሳ ጉዳይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 9 እና 231 (1) (ለ) እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዝገቦች በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ጉዳይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን የሚወድቅ መሆኑ አለመሆኑን ለመለየት

አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የማይንቀሳቀስ ንብረት በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ ከመሆኑ በተጨማሪ አመልካች እና ተጠሪ የኦሮሚያና አዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ስለመሆናቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በይፋ ባልተቋቋባቸው ክልሎች የፌዴራል ጉዳይ በውክልና የሚታይ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የስረ ነገር ስልጣኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቢሆንም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ በመሆኑ መታየት ያለበት በኦሮሚያ ክልል ንብረቱ የሚገኝበት የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ ስለመሆኑ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(4) ያስገነዝበናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይሁን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስረ ነገር ስልጣን የሌላቸው መሆኑን መገንዘብ ሲገባቸው ይህንን በማለፍ ግራ ቀኙን በማከራከር ፍርድና ትዕዛዝ መስጠታቸው በህጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖራቸው የሰጡት ፍርድና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ነው ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 63738 በ29/11/2008 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 185671 በ29/06/2009 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ በመሆኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡ ይሁንና የአሁኑ ተጠሪ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብታቸው ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት በ2/08/2009 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ